መብቶትን ይወቁ

የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብአዊ መብቶች እና የፍትሃዊነት ፕሮግራሞች ጽ / ቤት

ማንነታችን

የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብቶችና የፍትሃዊነት ፕሮግራሞች ጽሕፈት ቤት (OHREP) በሥራ ቅጥር፣ በመኖሪያ ቤት፣ በሕዝብ ማመቻቻ፣ የግል ትምህርት እና ብድር መድልዎ የሚከለክለውን የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌን እና የፌርፋክስ ካውንቲ ፍትህ ያለበትን የቤቶች አሰጣጥ ህግን ያጠናክራል። OHREP በፌርፋክስ ካውንቲ ውስጥ መድልዎ እንደተፈፀመበት በሚያምን ማንኛውም ሰው የቀረቡትን አቤቱታዎች ይቀበላል፣ እና ይመረምራል።

ጽህፈት ቤታችን የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌን እና ፍትሃዊ የቤቶች ህግን ማክበርን በተመለከተ ለዜጎች፣ ለአሰሪዎች፣ ለድርጅቶች፣ ለንግድ ድርጅቶች እና በፌርፋክስ ካውንቲ ውስጥ የቤቶች ልማት ኢንዱስትሪን በተመለከተ የትምህርት አገልግሎቶችን ይሰጣል።

COUNTY OF FAIRFAX
1742
VIRGINIA

ሕጉን ይወቁ

የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ እና የፌርፋክስ ካውንቲ ፌር የቤቶች ህግ ከሚከተሉት በአንዱ በአባልነታቸው መሠረት በማንኛውም ሰው ላይ መድልዎ እንዳይኖር ይከለክላሉ።

- ☑ ዘር፣
- ☑ ቀለም
- ☑ ሃይማኖት
- ☑ ጾታ፣
- ☑ ወሲባዊ ዝንባሌ
- ☑ የሥርዓተ-ፆታ ማንነት
- ☑ የጋብቻ ሁኔታ
- ☑ የቤተሰብ ሁኔታ *
- ☑ እርግዝና
- ☑ ማጥባት ጨምሮ፣ ልጅ መውለድ ወይም ተዛማጅ የሕክምና ሁኔታዎች **
- ☑ እድሜ፤
- ☑ የአካል ጉዳት
- ☑ የገንዘብ ምንጭ *
- ☑ የአርበኝነት ሁኔታ
- ☑ የመጠበት አገር

* የመኖሪያ ቤትን በተመለከተ ይሆናል።

** የመኖሪያ ቤትን አይመለከትም።

መብቶትን ይወቁ

የእርስዎ ህጋዊ መብቶች እንደተጣሱ እርግጠኛ አይደሉም? የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ እና የፌርፋክስ ካውንቲ ፍትህ ያለበት የቤቶች ህግ በሚከተሉት ውስጥ መድልዎን ይከለክላሉ፣

ሥራ፣ አራት ወይም ከዚያ በላይ ሠራተኞች ያሉት ቀጣሪ፣ የሥራ ስምሪት ድርጅት፣ በአንድ የተጠበቀ ክፍል አባልነትትዎ መሠረት የእርስዎን የእድገት ደረጃ ቀንሶአል፣ አባርዎታል፣ አስፈላጊውን ማማቻቻ ከልክልዎታል ወይም የደረጃ ዕድገት ከልክልዎታል።

የህዝብ ማማቻቻዎች፣ በተጠበቀ መደብ ውስጥ ባለዎት አባልነት ላይ በመመርኮዝ አንድ ለህዝብ ክፍት የሆነ ቦታ ባለቤት፣ ሥራ አስኪያጅ / ተቆጣጣሪ ወይም ሠራተኛ ቤቶችን እና ማንኛውንም ተዛማጅ መገልገያዎችን፣ ልዩ መብቶችን ወይም ሌሎች ጥቅሞችን በሙሉ እንዳያገኙ ከልክልዎታል።

ብድር፣ በተጠበቀ መደብ ውስጥ አባል በመሆንዎ ምክንያት አንድ ባንክ፣ የፋይናንስ ድርጅት፣ አበዳሪ ኩባንያ፣ የአበዳሪ ተቋም ወይም የንግድ ሥራ ብድርዎን ወይም ሌሎች ብድርን የሚመለከቱ አገልግሎቶችን አቅርቧል፣ ከልክሏል ወይም አቋርጧል።

የግል ትምህርት፣ በተጠበቀ መደብ ውስጥ አባል በመሆንዎ ምክንያት አንድ የግል የትምህርት ተቋም ወይም ወኪሎቹ፣ ሠራተኞቹ፣ ባለቤቶቹ ወይም አስተዳዳሪዎቹ በዚያ ተቋም ውሎች፣ ሁኔታዎች፣ ጥቅሞች፣ መብቶች ወይም አገልግሎቶች በተለየ ሁኔታ አስተናግድዎታል።

መኖሪያ ቤት፣ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በሽምግልና (ዕድሜዎ 55 ወይም ከዚያ በላይ)፣ በቤተሰብ ሁኔታ (እድሜአቸው ከ18 በታች የሆኑ ልጆች ያላቸው ቤተሰቦች)፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታ ዝንባሌ፣ በፆታ ማንነት፣ በአርበኛ ሁኔታ፣ በገንዘብ ምንጭ ወይም በአካል ጉዳተኝነት መሰረት የቤት ወይም ሌሎች የቤት-ነክ ግብይቶች ሸያጭ፣ ኪራይ፣ ወይም ፋይናንስ ተከልክለዋል። መሬት ወይም ሕንጻዎችን ከያዘ ንብረት (ሪል እስቴት) ወይም ከሪል እስቴት ጋር በተዛመደ ግብይት በአድሎአዊነት ማስታወቂያ ወይም በማንኛውም የአድልዎ መግለጫ ውስጥ ገብተዋል፣ ወይም ፍትሃዊ የቤት መብት በመጠቀም ወይም ሌሎች ያንን መብት እንዲጠቀሙ በመርዳት ዛቻ፣ ማስገደድ፣ ማስፈራራት ወይም ጣልቃ ገብነት አጋጥምዎታል።

በቀል፣ አንድ ሰው - እንደ አሰሪ፣ የንግድ ሥራ ባለቤት ወይም አከራይ - የመድልዎ አቤቱታ በማቅረባዎ ወይም በምስክርነት፣ በመርዳት ወይም በማንኛውም ምርመራ፣ ሂደት ወይም መስማት በመሳተፍዎ ላይ የበቀል እርምጃ ይወስዳል።

ቅሬታ እንዴት እንደሚቀርብ

በሕገ-ወጥ መንገድ አድልዎ ደርሶብኛል ብለው የሚያስቡ ከሆነ፣ አድልዎ ተፈጽሞብኛል ካሉበት ቀን ጀምሮ በ365 ቀናት ውስጥ ለ OHREP አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። ቅሬታ ለማቅረብ ወይም አቤቱታ ስለማቅረብ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ-

ይደውሉልን፣ 703-324-2953, TTY 711

የእኛን ድረ ገጽ ይጎብኙ፣ fairfaxcounty.gov/humanrights

ቢሮአችንን ይጎብኙ፣:
Fairfax County Government Center
12000 Government Center Parkway, Suite 318
Fairfax, VA 22035-0093

ቅሬታ ለማስገባት ምንም ክፍያ የለም።

አድልዎ ተፈጽሞብኛል ባሉበት በ365 ቀናት ውስጥ ቅሬታ መቅረብ አለበት።

ቅሬታን ለማቅረብ የሚያስፈልጉ 6 ደረጃዎች

ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በምርመራው ሂደት ውስጥ የሚከተሉትን እርምጃዎች መጠበቅ አለብዎት።

1. የመግቢያ መጠይቅ ያጠናቅቃሉ።
2. አቤቱታውን ለማዘጋጀት አንድ መርማሪ ከእርስዎ ጋር በስልክ ወይም በአካል ቀርቦ ቃለ መጠይቅ ያደርጋል።
3. የአቤቱታ ቅጽ ያዘጋጃሉ እና ይፈርማሉ። +
4. መርማሪው ለምላሽ ሰጭው ያሳውቃል።
5. እውነታዎችን ለማወቅ ጥልቅ ምርመራ ይካሄዳል።
6. OHREP ማስረጃው የርስዎን ጥያቄ ይደግፍ ወይም አይደግፍ እንደሆነ ይወስናል።

* አቤቱታዎ እርስዎ እስኪፈርሙ ድረስ እንደ “ክስ” አይቆጠርም፣ እና OHREP ቅሬታውን በተመለከተበት ቀን ተቀብሎ ማህተም አድርጓል።

እኛ እንዴት እንደምናገለግልዎ

OHREP የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌን እና የፌርፋክስ ካውንቲ ፍትህ ያለበት የቤት የቤቶች ህግን የሚያስፈፅም ገለልተኛ፣ ሀቅ ፈላጊ፣ አስተዳደራዊ ድርጅት ነው። የሕግ ውክልና አናቀርብም።

መስሪያ ቤታችን መድልዎችን በሚከተለው ሁኔታ ይዳስሳል፣

- ጉዳዮችን በመቀበል፣ በማጣራት፣ በሽምግልና፣ በምርመራ፣ በእርቅ፣ እና በአደባባይ ችሎቶች መፍታት።
- በፌርፋክስ ካውንቲ ውስጥ የመድልዎ መጠን ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ መሞከር።
- የቤቶች እና የሥራ አድልዎን ጨምሮ በሲቪል መብቶች ርዕሶች ላይ ተናጋሪዎችን እና ፕሮግራሞችን ማቅረብ።

እንዲሁም አድልዎን በተመለከተ በድረ-ገፃችን እና በጥያቄ ነፃ ህትመቶችን ማግኘት ይችላሉ።

የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብአዊ መብቶች እና የፍትሃዊነት ፕሮግራሞች ጽ / ቤት

12000 Government Center Parkway, Suite 318
Fairfax, VA 22035-0093
ስልክ፣ 703-324-2953፣ መስማት ለተሳናቸው 711
fairfaxcounty.gov/humanrights

አንድ ፌርፋክስ ካውንቲ፣ ቫ.፣ ህትመት | ሰኔ 2018

የፌርፋክስ ካውንቲ በሁሉም የካውንቲ መርሃግብሮች፣ አገልግሎቶች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ የአካል ጉዳትን መሠረት ያደረገ አድልዎን ለመከላከል ቁርጠኛ ነው። በተጠየቁ ጊዜ ተመጣጣኝ የADA ማመቻቻና እና አማራጭ የመረጃ ቅርፀቶች ይቀርባሉ።

እ.ኤ.አ. መስከረም 2020 (Amharic)